# እንኳን ወደ ህዝብ ቤተ-መጻህፍት በደህና መጡ

የህዝብ ቤተ-መጻህፍት ለሁሉም የኮሚኒቲ ህብረተ-ሰብ ተጠቃሚ ክፍት ነው። በዚህ ቤተ-መጻህፍት እርስዎንና ቤተሰብዎን የሚፈልጉትን መረጃ ማግኘት፡ ማንበብ ወይም ማጥናት፡ ጥያቄዎች መጠየቅ፡ መጻህፍት መዋስ፡ እና የመሳሰሉትን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ።

## በቤተ-መጻህፍት ውስጥ እርስዎና ቤተሰብዎ የሚከተሉትን ኣገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡



**የቤተ-መጻህፍት ንብረት መዋስ፡**

- እግሊዝኛ ለመማር የሚያገለግሉ
- ዲ.ቪ.ዲ፡ የሙዚቃና በሲ.ዲ የሰፈሩ መጻህፍት
- መጻህፍት፡ መጽሔቶች እና ሌሎች




**ኮምፒዩተር መጠቀም፡**

በአብዛኞቹ ቤተ-መጻህፍት ለኢ.መይል እና ለኢንተርነት የሚያገለግሉ ኮመፒዩተሮች አሉ። አንዳንድ ቤተ-መጻህፍት ደግሞ ደብዳቤዎች ለመጻፍና ቋንቋ ለመማር የሚያገለግሉ ኮምፒዩተሮች ይገኝባቸዋል።



**ኢንተርነት መጠቀም፡**

አንዳንድ ቤተ-መጻህፍት ልዩ ኦን-ላይን ማተሪያልና ዳታ-በይዝ ይገኝባቸዋል። በኮምፒዩተር ላይ መጻህፍት፡ መጽሔቶችና ጋዜጣዎች፡ማንበብና ማዳመጥ ይቻላል። የተለያዩ ኦን-ላይን የሚገኙ ማተሪያሎች ስለ የትምህርት-ቤት ፕሮጀክቶች፡ የጤና ጥበቃ መረጃዎች እና የመሳሰሉትን ነገሮች ይገኙባቸዋል።



**በተለያዩ ቛንቋዎች የተጻፉ መጻህፍት እና መጽሔቶች ማግኘት፡**

አንዳንድ ቤተ-መጻህፍት በተለያዩ ቋንቋዎች የተጻፉ መጻህፍት፡ መጽሔቶችና ጋዜጣዎች ይገኙባቸዋል። የበለጠ መረጃ ለማግኘት ለቤተ-መጻህፍት ሰራተኛ ይጠይቁ።



**በቤተ-መጻህፍት የተዘጋጁ ፕሮግራሞች መሳተፍ፡**

ቤተ-መጻህፍት ለልጆች፡ ለወጣቶች፡ ለጎረምሶች እና ለቤተ-ሰብ የሚያገለግሉ ፕሮግራሞች፡ትምህርቶች እና መደቦች ያወጣሉ። ልጆቻቹ እየተዝናኑ እንዲማሩ ወደ ቤተ-መጻህፍት ያላኩዋቸው። አብዛኞቹ ቤተ-መጻህፍት፡ የመጻህፍት ክለብ፡ ለጉረምሶች የሚያገለግል የኮምፑተር ትምህርት እና ሌሎች ፕሮግራሞች ያዘጋጃሉ።ምን ምን ፕሮግራሞች እንደሚገኙባቸው ለማወቅ፡ ለቤተ-መጻህፍት ሰራተኛ ይጠይቁ።



**ለጥያቄዎቻቹ መልስ ማግኘት፡**

የቤተ-መጻህፍት ሰራተኞች ለሁሉም አይነት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ያግዝዋቹሃል። ብቻ ይጠይቁ!



**አጠገብዎ የሚገኝ ቤተ-መጻህፍት ማግኘት፡**

በማኒቶባ ከአንድ መቶ በላይ የህዝብ ቤተ-መጻህፍት አሉ።

**ዊኒፔግ የህዝብ ቤተ-መጻህፍት**
የህዝብ ቤተ-መጻህፍት
ሚለኒዮም ቤተ-መጻህፍት (ዋናው ጽህፈት-ቤት)
251 ዶናልድ ስትሪት፣ ዊኒፔግ
**ስ.ቁ.** 204-986-6450
**ዌብ-ሳይት፡** winnipeg.ca/library
በሃያ ቦታዎች ቤተ-መጻህፍት አሉን። ሚለኒዮም ቤተ-መጻህፍት ከሁሉም ትልቅ ሆኖ ከ650 000 በላይ የሚሆኑ መጻህፍት፡ ከሰላሳ በላይ ቋንቋዎች የተጻፉ ይገኙበታል።

**የምዕራብ ማኒቶባ  አጥብያ ቤተ-መጻህፍት**
ብራንደን ቤተ-መጻህፍት (ዋናው ጽህፈት-ቤት)
710 ሮሰር አቨኑ ፣ብራንደን
**ስ.ቁ.**: 204-727-6648
**ዌብ-ሳይት፡** wmrl.ca
በካንበሪ፡ በኒፓዋ፡በ ግለንቦሮ እና በሀርትነይ ቤተ-መጻህፍት አሉን።

**የደቡብ ሰንትራል አጥብያ ቤተ-መጻህፍት**
ዊንክለር ቤተ-መጻህፍት (ዋናው ጽህፈት-ቤት)
160 መይን ስትሪት ፣ ዊንክለር
**ስ.ቁ.** 204-325-7174
**ዌብ-ሳይት፡** scrlibrary.mb.ca
በአልቶና፡ በሞርደን እና በሚያሚ  ቤተ-መጻህፍት አሉን።

**ጄክ ኢፕ ቤተ-መጻህፍት**
255 ኢልመደይል ስትሪት፣ ስቴንባች
**ስ.ቁ.** 204-326-6841
**ዌብ-ሳይት፡** jakeepplibrary.com

ሌሎች በማኒቶባ ለሚገኙ የህዝብ ቤተ-መጻህፍት ለማግኘት በስ.ቁ.   1-800-252-9998 የደውሉ (ስልኩ ለመደወል በነጻ ነው።)
**ዌብ-ሳይት፡** gov.mb.ca/chc/pls/index.html

## የቤተ-መጻህፍት ካርድ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?፡

የቤተ-መጻህፍት ካርድ የቤተ-መጻህፍቱ አባል እንደሁኑ ያሳያል።  አጥቢያዎ በሚገኘው ቤተ-መጻህፍት መታወቂያ ወረቀት ይዘው በመሄድ የቤተ-መጻህፍት ካርድ ማግኘት ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ የቤተ-መጻህፍት ካርድ በነጻ ማግኘት ይቻላል። አባል ለመሆን ለቤተ-መጻህፍት ሰራተኛ ይጠይቁ።

- ለመታወቂያ የሚያገለግሉ እንደ  መንጃ ፈቃድ፡ የማኒቶባ ሄልዝ ካረድ፡ ወይም አድራሻዎ ያለበት ደብዳቤ ሊሆኑ ይችላሉ።
- የቤተ-መጻህፍት ካርድ  በጥንቃቄ መያዝ አለበት። ድንገት ካርዱ ከጠፋ ለቤተ-መጻህፍቱ ያሳውቁ።

## የቤተ-መጻህፍት ማተሪያል  እንዴት መዋስ እችላለሁኝ?፡

- በቤተ-መጻህፍት ያሉ አብዛኞቹ ማተርያሎች መዋስ ይቻላል። መጻህፍት ከቤተ-መጻህፍቱ ሲዋሱ መመለስ ያለበት ቀን ይጻፍበታል። የተዋሱት ማተሪያል በቀኑ መመለስ አለበት።
- ለሌሎች ተጠቃሚዎች እንዲያገለግል የተዋሱትን ማተሪያል ሳይበላሽ እንዳለበት መመለስ ይኖርበታል።

## መጽሐፍ ለመመለስ ከዘገየሁኝሳ?፡

- መጽሐፍ ዘግይቶ መመለስ መቀጮ አለበት።
- የተዋሱት ማተሪያል ረዘም ላለ ጊዜ ማቆየት የቻላል። እንዴት ማራዘም እንደሚቻል ለማወቅ ለቤተ-መጻህፍት ሰራተኛ ይጠይቁ።

## አጥቢያዎ የሚገኝ ቤተ-መጻህፍት፡

Manitoba · Winnipeg · Winnipeg Public LIBRARY · BIBLIOTHÈQUE publique de Winnipeg

Jan 2011